


# አስማሚ ተባብሮ የመታገያ
# አጀንዳችን ምን ይሁን?

## “ዘላቂ ሰላም እና ዴሞክራሲ በአዲስ የሽግግር ሒደት”

**ልደቱ አያሌው**

**ሐምሌ 28 2016 ዓ.ም**

# አስማሚ ተባብሮ የመታገያ አጀንዳችን ምን ይሁን?

## “ዘላቂ ሰላም እና ዴሞክራሲ በአዲስ የሽግግር ሒደት”

## መግቢያ

ከአንድ ወር በፊት ለውይይት መነሻነት ባቀረብኳቸው የአገራችንን የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በሚገመግሙ እና የሽግግር ሒደት አስፈላጊነትን በሚመለከቱ ሁለት ሰነዶች ዙሪያ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን 33 ውይይቶች ተካሒደዋል። በእነዚህ ውይይቶችም 53 ታዋቂ እና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰዎች ተሳትፈዋል። በዚህ የውይይት ሒደትም አምስት ርዕሰ-ጉዳዮች ማለትም፡-

1. የሽግግር መንግስት አስፈላጊነት፣
2. ብልፅግና ፓርቲ በሽግግሩ ሒደት የሚኖረው ተሳትፎ፣
3. የሰላማዊ የትግል ስልት አዋጭነት፣
4. የብሄርተኛነት ፖለቲካ መዋቅራዊ መሆን እና
5. የምርጫ 2018 ተሳትፎ ጉዳይ በጐላ ሁኔታ አወዛጋቢ እና አከራካሪ ርዕሰ ጉዳዮች ሆነው ታይተዋል።

በእነዚህ አምስት አከራካሪ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ቅዳሜ July 20/2024 **“ለጋራ የህልውና አደጋ የጋራ መድህን መሻት”** በሚል ርዕስ የበይነ-መረብ የመቋጫ ውይይት(‘ዌቢናር’) ለሰባት ሰዓታት ተካሂዷል። በዚህ ውይይት 26 የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት እና የብሄር ማንነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን በአከራካሪ ጉዳዮቹ ላይ ያላቸውን ዕይታ እና አቋም በንግግር አጋርተዋል። ከ150 በላይ የሆኑ ሰዎች ደግሞ በቀጥታ የስብሰባው ተካፋይ የሆኑ ሲሆን ውይይቱ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በቀጥታና በቅጂ ለሕዝብ ተላልፏል። ይሕንንም ተከትሎ መገናኛ ብዙሀንም ሆኑ በፖለቲካ ረገድ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑ ሰዎች ለውይይት በቀረቡት ሰነዶች ላይ ለመሳተፍ ያሳዩት ፍላጐት እና ተነሳሽነት ከተጠበቀው በላይ አበረታች ሆኖ ተገኝቷል። በሒደቱም ለውይይት ከቀረቡት አጀንዳዎች ውስጥ በየትኛዎቹ እንደምንስማማ፣ በየትኞቹ ደግሞ እንደምንለያይና የልዩነታችን መጠንም እስከምን ድረስ እንደሆነ ጥሩ እና በአንጻራዊነት ከ’ስከዛሬው የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ተችሏል።

እንዲህ አይነቱን የውይይት ሒደት በስፋት ማካሄድ ያስፈለገው በምክንያት ነው። የወቅቱ የፖለቲካ ትግል ተጠናክሮ ካልወጣና የአገዛዙን የጥፋት መንገድ ማስቆም እስካልቻለ ድረስ አገሪቱ እና ሕዝቡ ከህልውና ጥፋት መዳን አይችሉም። አገሪቱን እና ሕዝቡን ከህልውና ጥፋት መታደግ የሚጠበቅባቸው ተቃዋሚ ኃይሎች የትግል ትብብር ፈጥረው ተጠናክረው ለመውጣት ደግሞ የጠራ የመተባበሪያ አጀንዳ መያዝ ያስፈልጋቸዋል። እናም የዚህ የውይይት ሒደት አስፈላጊነት የመነጨው በዋናነት የትግል የመተባበሪያ አጀንዳዎችን ለይቶ ለማዎቅ፣ አውቆም በአጀንዳዎቹ ዙሪያ ለመተባበር ካለ ጽኑ ፍላጐት ነው።

በዚህም ምክንያት በውይይቱ ሒደት ጐልተው የወጡትን አምስቱን አከራካሪ ርዕሰ-ጉዳዮች በተመለከተ ቀጣይ ውይይቶች ማካሄድና በተወያዮች ዙሪያ ያለውን የአስተሳሰብ ልዩነት እና አንድነት በአግባቡ መለካት እና ማዎቅ አስፈላጊ ነበር። የሐምሌ 12ቱ የሙሉ ቀን የበይነ-መረብ ውይይት የተካሄደው ከዚህ ዓላማ በመነጨ ፍላጐት ነው። ከዚህ የሙሉ ቀን ውይይት በፊት 151 ሰዎች

በአከራካሪ ጉዳዮቹ ላይ ስለአላቸው አቋም የቅድመ-ውይይት (Pre-Forum) ድምፅ በጉግል ፎረም (Google Forum) በኩል በተዘጋጀው ዲጅታል ቅጽ ድምጻቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል። የውይይቱ ሒደት በተሳታፊዎች የቀደመ አስተሳሰብ ላይ የፈጠረውን አንደምታ ለመለካት ይቻል ዘንድም ከውይይቱ በኋላ የድህረ-ውይይት (Post-Forum) ድምፅ በድጋሚ እንዲሰጥ ተደርጓል። በውይይቱ ላይ ዕይታቸውን በንግግር ያካፈሉት 26 ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎችም በአምስቱ አከራካሪ ጥያቄዎች ላይ የያዙትን አቋም በተመሳሳይ መንገድ ለመሰብሰብ እና ለማዎቅ ተችሏል።

# 1.የአጀንዳ ልየታው ውጤት

በዚህ የጋራ አጀንዳን የመለካት እና ለይቶ የማወቅ ሙከራ በጉግል ፎረም (Google Forum) በኩል ከተሰራጨው ዲጅታል ቅጽ የተገኘው ውጤት በጥቅሉ የሚከተለውን ይመስላል።

| 1.1 የተሳታፊዎች የቅድመ እና ድሕረ-ውይይት የድምፅ ውጤት | | እስማማለኹ | አልስማማም | ለመወሰን እቸገራለኹ |
|---|---|---|---|---|
| በሽግግር መንግስት አስፈላጊነት | ቅድመ | 89.4% | 3.6% | 7% |
| | ድሕረ | 92.5% | 2.5% | 5% |
| | ልዩነት | 3.1% | -0.9% | -2% |
| በብልፅግና ፓርቲ የሽግግር መንግስት አካል መሆን | ቅድመ | 70.2% | 11.9% | 17.9% |
| | ድሕረ | 75% | 14.1% | 10.9% |
| | ልዩነት | 4.8% | 2.2% | -7% |
| በሰላማዊ ትግል አዋጭነት | ቅድመ | 75.5% | 9.9% | 14.6% |
| | ድሕረ | 73.8% | 6.6% | 16.8% |
| | ልዩነት | -1.7% | -3.3% | 2.2% |
| የብሄርተኛነት ፖለቲካን መዋቅራዊ መሆን በማስቀረት | ቅድመ | 88.7% | 5.3% | 6% |
| | ድሕረ | 86.9% | 7% | 6.1% |
| | ልዩነት | -1.8% | 1.7% | 0.1% |
| በ2018 ዓ.ም ምርጫ ተሳታፊ በመሆን | ቅድመ | 64.9% | 14.6% | 20.5% |
| | ድሕረ | 68.2% | 21.5% | 10.3% |
| | ልዩነት | 3.3% | 6.9% | -10.2% |

| 1.2 የሐሳብ አቅራቢዎች የድምፅ ውጤት | እስማማለኹ | አልስማማም | ለመወሰን እቸገራለኹ |
|---|---|---|---|
| በሽግግር መንግስት አስፈላጊነት | 85.2% | 11.1% | 3.7% |
| በብልፅግና ፓርቲ የሽግግር መንግስት አካል መሆን | 66.7% | 25.9% | 7.4% |
| በሰላማዊ ትግል አዋጭነት | 63% | 14.8% | 22.2% |
| የብሄርተኛነት ፖለቲካን መዋቅራዊ መሆን በማስቀረት | 66.7% | 14.8% | 18.5% |
| በ2018 ዓ.ም ምርጫ ተሳታፊ በመሆን | 51.9% | 25.9% | 22.2% |

# 2. የተገኘው አጠቃላይ ውጤት አንደምታ

2.1. ለውይይት በቀረቡት ሁለት ሰነዶች ውስጥ አከራካሪ ሆነው የተገኙት አምስቱም ነጥቦች በውይይቱ ላይ አቋማቸውን እንዲያጋሩ በተመረጡት ሰዎችም ሆነ በውይይቱ ተሳታፊዎች ዘንድ ሁሉም የአብላጫ ድምፅ ድጋፍ አግኝተዋል። *ይሁንና ከሐሳብ አቅራቢዎቹ የተገኘው ድጋፍ ከተሳታፊዎቹ ከተገኘው ድጋፍ በአማካይ ከ7 እስከ 19% ያነሰ ሆኖ ታይቷል።* ማለትም አከራካሪ ነጥቦቹ በውይይቱ ላይ አቋማቸውን እንዲያጋሩ ከተመረጡት ተፅዕኖ ፈጣሪ ሰዎች በላይ በተሳታፊዎቹ ዘንድ ድጋፍ አግኝተዋል።

2.2. ከአከራካሪ ርዕሰ-ጉዳዮቹ መካከል በከፍተኛ መጠን ድጋፍ ያገኘው "አገሪቱን ከህልውና ጥፋት ለማዳን ሁሉን-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት ማቋቋም ያስፈልጋል" የሚለው ሐሳብ ነው። ይህ ሐሳብ በውይይቱ ዕለት ሐሳብ አቅራቢ በነበሩ ሰዎች ዘንድ 85.2% ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ ድምፅ በሰጡ ተሳታፊዎች ዘንድ ደግሞ 92.5% ድጋፍ አግኝቷል።

3.3. ከአከራካሪ ርዕሰ-ጉዳዮቹ መካከል በአነስተኛ መጠን የአብላጫ ድምፅ ያገኘው "በ2018 ዓ.ም በአገራችን ምርጫ የሚካሄድ ከሆነ ተቃዋሚዎች መሳተፍ ይኖርባቸዋል" የሚለው ሐሳብ ነው። ይህ ሐሳብ ድምፅ በሰጡ ተሳታፊዎች 68.2% ድጋፍ ያገኘ ሲሆን በውይይቱ ላይ ሐሳብ በአቀረቡ ሰዎች ዘንድ ያገኘው ድጋፍ ግን 51.9% ብቻ ነው።

3.4. የተካሄደው የአንድ ሙሉ ቀን ውይይት *በተሳታፊዎች ወይም በድምፅ ሰጭዎች አመለካከት ላይ አንፃራዊ የሆነ ለውጥ እንዳመጣ* ታይቷል። ከአምስቱ አከራካሪ ነጥቦች ውስጥ አራቱ በድህረ-

ውይይቱ የድምፅ አሰጣጥ የድጋፍ መጠናቸው በአማካይ ከ2 እስከ 5% ጨምሯል። ነገር ግን "የብሄርተኛነት ፖለቲካ መዋቅራዊ መሆን አይገባውም" የሚለው ሐሳብ በ1.8% ድጋፉ ቀንሷል። በተጨማሪም "ለመወሰን እቸገራለሁ" የሚለው ድምፅ ከ2 እስከ 10% በሶስት ጉዳዮች ላይ የቀነሰ ሲሆን በቀሪዎቹ ሁለት ጉዳዮች ላይ ግን ከ0.1 እስከ 2.2% ጨምሯል። በዚህ ረገድ ሰፊ ለውጥ የታየው የ2018 ምርጫ ተሳትፎ ጉዳይ ሲሆን ከ10 በላይ የሆኑ ድምፅ ሰጭዎች ከውይይቱ በኋላ የቀደመ አቋማቸውን በመቀየር "ለመወሰን እቸገራለሁ" ወደሚል አቋም ተሸጋግረዋል።

3.5. "ለመወሰን እቸገራለሁ" የሚል ድምፅ የበለጠ የተሰጠው ከተሳታፊዎች ይልቅ በሐሳብ አቅራቢ ሰዎች ነው። ከ5 እስከ 16.8% የሚሆኑ ተሳታፊዎች በተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ "ለመወሰን እንቸገራለን" የሚል ድምፅ የሰጡ ሲሆን፣ ከ3.7 እስከ 22.2% የሆኑ ሐሳብ አቅራቢዎች ደግሞ "ለመወሰን እንቸገራለን" የሚል ድምፅ ሰጥተዋል። ከዚህ የምንረዳው የዕለቱ ውይይት በድጋፍ፣ በተቃውሞም ሆነ አቋም ለመያዝ በመቸገር ረገድ የተወሰነ ለውጥ ያመጣ መሆኑን ነው።

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ በአፅንኦት ለመግለፅ እንደተሞከረው በአገራችን ወቅታዊ ፖለቲካ አወዛጋቢ የሆኑትን ጉዳዮች ለይቶ የማወቁ እና የልዩነቱን መጠን በአግባቡ የመለካቱ አስፈላጊነት የመነጨው በዋናነት የተቃዋሚውን ጐራ ትግል ወደ ትብብር ለማምጣት የሚያበቁ የጋራ መለስተኛ (Minimum) አጀንዳዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ነው። ከዚህ አኳያ የውይይቱ ሒደት ምን ፋይዳ እንደነበረው በሚከተለው አግባብ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

**አንደኛ፡** በውይይቱ ሒደት የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት እና የብሄር ማንነት ያላቸው አካላት በጋራ ተገናኝተው ለመወያየት ያሳዩት ፈቃደኛነትና ተሳትፎ ወደ የጋራ የትግል ትብብር ለመሄድ በራሱ አንድ አበረታች ቁም-ነገር ሆኖ ተገኝቷል።

**ሁለተኛ፡** የተወሰደው ናሙና አነስተኛ ከመሆኑ አኳያ የዳሰሳ ጥናቱ 'ትክክለኛውን (Accurate) ውጤት ያሳያል!' ባይባልም በአምስቱም አወዛጋቢ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የአብላጫ ድምፅ መገኘቱ፣ ከአንድ ጉዳይ በስተቀርም በሌሎቹ ጉዳዮች ላይ የተገኘው የአብላጫ ድምፅ ከፍተኛ ሊባል የሚችል-ማለትም በተሳታፊዎች ዘንድ ከ68.2 እስከ 92.5%፣ በሐሳብ አቅራቢዎች ዘንድ ደግሞ ከ63% እስከ 85.2% መሆኑ ወደፊት ተከታታይ እና ተመሳሳይ ውይይቶች ቢካሄዱ የተሻለ መቀራረብ እና መግባባት ሊፈጠር እንደሚችል ተስፋ ያጫረ ሆኗል። በተለይም የሽግግር መንግስት አስፈላጊነትን በተመለከተ ሐሳብ አቅራቢዎች 85.2%፣ ተሳታፊዎች 92.5% መደገፋቸው ህልውናችንን ከጥፋት ለመታደግ አጀንዳው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና በሒደትም ቢያንስ በፖለቲካ ልሂቃኑ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ እንደመጣ በግልፅ ያሳያል።

**ሦስተኛ፡** በተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ውጤታማ የትግል ትብብር ለመፍጠር በቁልፍ አጀንዳዎች ላይ አብላጫ ድምፅ ከማግኘትም ባለፈ የተሟላ ስምምነት (Consensus) ላይ መድረስን ይጠይቃል። ከዚህ አኳያ በአምስቱ አወዛጋቢ ጉዳዮች ላይ የሚታዩት ልዩነቶች የቱንም ያህል የጠበቡ ቢሆኑም እነዚህ ልዩነቶች የትብብር ትግል በቀላሉና በምንፈልገው

ፍጥነት እንዳይፈጠር እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ። ከፍተኛ ድጋፍ ያገኘው የሽግግር መንግስት የማቋቋም ጥያቄ በአንፃራዊነት አንድ የተሻለ የመተባበሪያ አጀንዳ የመሆን ዕድል ያለው ቢመስልም በሐሳብ አቅራቢዎቹ ዘንድ 11.1% ተቃውሞ እና 3.7% "ለመወሰን እቸገራለሁ" የሚል አቋም የተያዘበት መሆኑን ስናይ ግን አጀንዳው አስተማማኝ ትብብር ለመፍጠር የሚያበቃ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም 11.1% ትንሽ ድርሻ መስሎ ቢታይም በዚህ ድርሻ ውስጥ የጐላ ማሕበራዊ መሰረት ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የእነሱ የትብብሩ አካል አለመሆን በዓላማው ስኬት ላይ ከባድ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊፈጥር ይችላል።

ስለዚህ ከአምስቱ አከራካሪ ርዕሰ-ጉዳዮች ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኘውን የሽግግር መንግስት የማቋቋም አስፈላጊነት ጨምሮ የሁሉንም ኃይሎች ሙሉ ፈቃደኛነት በማግኘት የጋራ የትግል መተባበሪያ ለመሆን የበቃ አጀንዳ አለ ማለት አይቻልም። ለውይይት በቀረቡት ሁለት ሰነዶች ውስጥ ሁላችንንም የሚያስማሙ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ያሉ ቢሆኑም አምስቱ ነጥቦች ግን ከውይይቱም በኋላ አከራካሪ ሆነው መቀጠላቸው የማይቀር ስለሆነ ከአጭር ጊዜ ግብ አንፃር የመተባበሪያ አጀንዳ ሊሆኑን አይችሉም።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በዚህ መጠን አብላጫ ድምፅ ያገኘ አጀንዳ የትግል ትብብር ለመፍጠር ካላስቻለን ሌላ ከዚህ የተሻለ የሚያስማማን አጀንዳ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ይሆናል። ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት የምንችለው በአንድ በኩል በእስካሁኑ የውይይት ሒደት በጋራ የተገባባንባቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች ወደፊት በማምጣት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት በተጨባጭና በዋናነት ያለበትን ችግር ለይተን በማወቅና የጋራ የመታገያ አጀንዳችን እንዲሆን በማድረግ ይሆናል።

# 3. ዋናው የመተባበሪያ አጀንዳችን ምን ይሁን?

## 3.1. ሰላም፡ እንደ ቀዳሚ አጀንዳ

መጠኑ ጠባብም ይሁን ሰፊ፣ ልዩነት የፈጠርንባቸውን አከራካሪ አጀንዳዎች የህልውና አደጋ ላይ በምንገኝበት በዚህ ወቅት የውዝግብ ማዕከል አድርጐ መቀጠል ወቅታዊ እና ጠቃሚ አይሆንም። ይልቁንም እነዚህን የልዩነት ርዕሰ-ጉዳዮች የየራሳችን የተናጠል አጀንዳ አድርገን ይዘን መቀጠላችን እንደተጠበቀ ሆኖ ሲቻል በውይይት እና በድርድር፣ ካልተቻለም በሕዝበ-ውሳኔ እና በሕዝብ ምርጫ ወደፊት ለመፍታት የሚያስችል ሰፊ የዴሞክራሲያዊ ሒደት ማዕቀፍ ላይ መስማማት ይኖርብናል። በፖለቲካ ኃይሎች ዙሪያ ባሉ እና የቱንም ያህል ጊዜ ወስደን ስንዎያይባቸው ብንከርም መተማመን ላይ የማንደርስባቸውን አጀንዳዎች ለጊዜው ወደ ጐን አስቀምጠን የሕዝቡን ወቅታዊ እና አንገብጋቢ ችግር ለይተን ብናውቅና የጋራ የመታገያ አጀንዳችን ብናደርገው የበለጠ ጠቃሚ እና አዋጭ ይሆናል።

በእኔ አመለካከት ለፖለቲካም ሆነ ለኢኮኖሚ ቀውስ የዳረገን የወቅቱ የሕዝባችን ቁጥር አንድ አንገብጋቢ ችግር የሰላም እጦት ነው። ዛሬ ላይ በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ ከጫፍ-ጫፍ

ብንሄድ በሰላም እጦት ያልተማረረ እና ኑሮው ያልተመሰቃቀለ ሕዝብ አናገኝም። በሕዝቡ የዕለት-ተዕለት ኑሮም ላይ ሆነ በዘላቂ ህልውናው ላይ ከፍተኛ አደጋ የደቀነበት የሰላም ዕጦት ነው። ሕዝቡ በሰላም ዕጦት የኢኮኖሚ፣ የማሕበራዊ እና የፖለቲካ ሕይወቱ አብዝቶ ከመመሰቃቀሉ የተነሳ አንፃራዊ ሰላም አግኝቶ በድህነት እሳና በአምባገነናዊ አገዛዝ ጭምር በጭቆና ስር ለመኖር የሚመርጥበት ከፍተኛ የመማረር ደረጃ ላይ ደርሷል። ስለዚህ የሰላም መፈጠርን ዋና የትግል ትብብር መፍጠሪያ አጀንዳ ማድረግ ተገቢና ጠቃሚ ይሆናል።

## 3.2. አዲስ የሽግግር ሒደት

የሰላም መኖሮ በራሱ አንድ ታላቅ ግብ ተደርጐ መቆጠር ያለበት ከመሆንም በላይ ለሌሎች የለውጥ ጥያቄዎች መሳካትም አስፈላጊ መደላድልና ዋና ቅድመ-ሁኔታ ነው። ይህ ታላቅ የሰላም አጀንዳ በሌሎች የለውጥ ተዛማጅ ሒደቶች ተደግፎ ካልመጣ በስተቀር ግን እንዲሁ ስለተመኘነውና ስለፈለግነው ብቻ በዘላቂነት ሊገኝ አይችልም።

በ2010 ዓ.ም በአገራችን ‘ተጀመረ!’ የተባለው የለውጥ ሒደት እንዳይመለስ ሆኖ መክሸፉ፣ ከእንግዲህም በስልጣን ላይ ባለው የብልፅግና አገዛዝ አገሪቱ ወደ በጐ ለውጥ የመሸጋገር ዕድል እንደሌላት ከመቸውም ጊዜ በላይ ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ስለሆነም አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላም በአገራችን እንዲመጣ ከተፈለገ አዲስ የሽግግር ሒደት ውስጥ መግባት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው።

በተካሄዱት የውይይት ሒደቶች በግልፅ እንደታየው በሽግግር መንግስት ጥያቄ ላይ ጥቂት ኃይሎች ልዩነት ያላቸው ቢሆንም በአዲስ የሽግግር ሒደት አስፈላጊነት ላይ ግን ልዩነት ወይም ተቃውሞ ያለው የፖለቲካ ኃይል የለም። ከራሱ ከብልፅግና ፓርቲ እና ከጥቂት አጫፋሪዎቹ በስተቀር የወቅቱ አገዛዝ አገሪቱን ከህልውና ጥፋት አድኖ ወደምንፈልገው በጐ ለውጥ ሊያሸጋግረን ይችላል የሚል ተስፋ ያለው የተቃዋሚ ኃይል የለም። እንኳንስ ተቃዋሚው ጐራ ራሱ ብልፅግና ፓርቲም “አገራዊ ምክክር አካሂዳለሁ” በማለት የማስመሰል ስራ ለመስራት የተገደደው አገሪቱን ወደሚፈለገው ለውጥ ማሸጋገር እንዳልቻለ ስለተገነዘበ ነው።

ስለዚህ ወደ በጐ ለውጥ ለመሸጋገር በቀዳሚነት አስፈላጊ የሆነውን የሰላም አጀንዳ ለማሳካት ወደ አዲስ የሽግግር ሒደት (የሽግግር መንግስት አላልኩም) መግባት የግድ አስፈላጊ ነው። የሚፈለገው ሰላም አስተማማኝ እና ዘላቂ በሆነ መጠን እንዲመጣም በአዲሱ የሽግግር ሒደት የሚከተሉት ልዩነት ልንፈጥርባቸው የማንችል እና የማይገባ ሁለት መሰረታዊ ሁነቶች መከናዎን ይኖርባቸዋል። እነሱም፡- አንደኛ፣ ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ መድረስና የወቅቱን ጦርነት ማቆም፤ ሁለተኛ፣ ህቀኛና ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የውይይትና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ማካሄድ ናቸው።

## 3.3 ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት

የሰላም አጀንዳ በአንድ በኩል የሕዝቡ ቀዳሚና አንገብጋቢ አጀንዳ በመሆኑ ላይ ከተግባባን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰላም ወደ በጐ ለውጥ ለመሸጋገር እና ከህልውና ጥፋት ለመዳን ዋና ቅድመ-ሁኔታ በመሆኑ ላይ ከተማመንን *እየተዋጉና እየተገዳደሉ ሰላምን ማምጣት አይቻልምና በሀቀኛ ድርድር ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ላይ መድረስ የግድ አስፈላጊ ነው።* ለዝግጅት ጊዜ ለመግዛት፣ ለተራ የፕሮፓጋንዳና የዲፕሎማሲ ጥቅም ለማግኘት የሚደረግ ሳይሆን ልባዊ የሆነ ድርድር በማካሄድ ጦርነትን ማቆምና ሰላምን ማስፈን ያስፈልጋል፣ ይቻላልም! ከጠባብ ግላዊ እና ቡድናዊ ሥሜት እና የጥቅም ፍላጐት ወጥተን ለጋራ ህልውናችን መቀጠል ትኩረት መስጠት ከቻልን ጦርነትን ማስቆም የማንችልበት ምክንያት የለም። የመንግስትም ሆነ የተቀናቃኝ ኃይሎች ታጣቂዎች ወደ ካምፕ እንዲገቡ፣ ከዚያም በሰላም ማስከበር ተግባር ላይ ሁሉም ስርዓት ባለው አግባብ እንዲሳተፉ ከተደረገና ሕጋዊ እና ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚችሉበት ሁኔታ ከተመቻቸ ወደ ተጨባጭና በጐ ለውጥ ለመሸጋገር የሚያበቃን ሰላም መፍጠር እንችላለን።

## 3.4 አገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት (አውድሒ)

የጦርነት ተዋናኝ የሆኑት ኃይሎች እንዲሁ መገዳደል ስለፈለጉ የሚዋጉ ሳይሆኑ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማንነት ወይም የህልውና ጥያቄ ስላላቸው የሚዋጉ ናቸው። እነዚህ ፈርጀ-ብዙ ጥያቄዎች የየራሳቸውን ልዩ መፍትሄ የሚፈልጉ እንጅ የተኩስ ማቆም ስምምነት ስለተፈረመ ብቻ መልስ ሊያገኙ የሚችሉ አይደሉም። ስለዚህ እነዚህን ጥያቄዎች አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል ሁሉን-አቀፍ የውይይትና የድርድር ሒደት /National Dialogue/ ማካሄድ ለዘላቂ ሰላም መምጣት የግድ አስፈላጊ ነው።

ሰሞኑን በልዩነት ርዕሰ-ጉዳይነት ስንወያይባቸው እና ስንከራከርባቸው የታዩ አምስት ነጥቦችም ሆኑ ሌሎች መሰረታዊ ልዩነቶቻችንን በዴሞክራሲያዊ አግባብ ማለትም በውይይትና በድርድር፣ በምርጫ ፉክክርም ሆነ በሕዝበ-ውሳኔ የመወሰን እድል ልናገኝ የምንችለው ሁሉን-አቀፍ፣ ሀቀኛና ግልፅነትን የተላበሰ ሀገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት በአዲስ የሽግግር ማዕቀፍ ማካሄድ ስንችል ነው። ለምሳሌ አሁን ላይ አወዛጋቢ የሆኑብን ሽግግር መንግስት ማቋቋም ያስፈልገናል ወይስ አያስፈልገንም? እርቅንና አገራዊ መግባባትን እንዴት መፍጠር እንችላለን? የሽግግር ጊዜ ፍትህን ማስፈን የምንችለው መቸና እንዴት ነው? ሕገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎች ማድረግ ያለብን እንዴትና መቼ ነው?"፤ "የፖለቲካ ምህዳሩ ለሁላችንም የተመቸ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት?"፣ "በአጠቃላይ የወደፊቷ ኢትዮጵያ እንዴት ትቀጥል?" በሚሉትና በሌሎችም ቁልፍ የልዩነት ጉዳዮች ዙሪያ ለአሉን ጥያቄዎች አስተማማኝ መፍትሄ ማግኘትና ሰላምን በብቃት እና በዘላቂነት ማስፈን የምንችለው ከፍ ሲል የተጠቀሰው ዓይነት አገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት (አውድሒ) በማካሄድ ነው።

እነዚህን ሰላምን በብቃት ለማስፈን በሚያስችሉንና ማንም ምክንያታዊ የሆነ የፖለቲካ ኃይል ልዩነት ሊፈጠርባቸው የማይችል ወይም የማይገባ ሁለት መሰረታዊ አጀንዳዎች "ሰፊ

ማዕቀፍ ሊሆን ይገባል!” ካልነው ከአዲስ የሽግግር ሒደት መፈጠር ጋር አጣምረን እና አጣጥመን እንደ ዋና የትግል የመተባበሪያ አጀንዳ ልንይዛቸውና ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

## ማጠቃለያ

በጥቅሉ የወቅቱን ትግል በብቃት ለማስተባበር እና ለማጠናከር እንዲቻል የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች በቅደም-ተከተል በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የጠራ አቋም መያዝና መግባባት ይኖርብናል።

1ኛ፦ አገሪቱ አሁን ላይ እየሄደች ባለችበት መንገድ ከቀጠለች ሰላም ማግኘትና ከህልውና ጥፋት መትረፍ እንደማትችል መተማመንና ሁሉን-አቀፍ ወደ ሆነ አዲስ እና ሀቀኛ የሽግግር ሒደት ለመግባት መስማማት፤

2ኛ፦ እውነተኛ ሰላም በአገሪቱ እንዲሰፍን የሚያስችል ሀቀኛ ድርድር በመንግስትና በሁሉም ታጣቂ ኃይሎች መካከል ተካሂዶ ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት እንዲፈረም እና ጦርነት እንዲቆም መስማማት፤

3ኛ፦ የተገኘውን ሰላም በዘላቂነት ለማፅናት እና አገሪቱን ከህልውና ጥፋት ለመታደግ የሚያስችል ሁሉን-አቀፍ አገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ለማካሄድ እና በዚህ ሒደት በሚደረስባቸው ውሳኔዎች ለመገዛት ሁላችንም አስቀድመን መስማማት ናቸው። እነዚህ ስምምነቶች በጥቅሉ “ዘላቂ ሰላም እና ዲሞክራሲ በአዲስ የሽግግር ሒደት” ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ።

በእኔ ዕይታ፣ በእነዚህ በዋናነት ሰላምንና የዴሞክራሲ ሒደትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ አለመስማማት የሚቻል አይመስለኝም። በቅድሚያ በሀቀኛ ድርድር የተኩስ ማቆም ስምምነት ተፈርሞ በአገራችን ጦርነት እስካልቆመ ድረስ አገሪቷ እና ሕዝቧ ከህልውና ጥፋት ሊድኑ ስለማይችሉ የሰላምን መኖር የሚቃዎም ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ለአገርና ለሕዝብ ደህንነት የምታገል ነኝ ሊል አይችልም። በተጨማሪም በልዩነት ጐልተው በወጡት አምስት ርዕሰ-ጉዳዮች እና በሌሎችም መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደቱ አሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ አግባብ እንዲወስን አለመስማማት ዴሞክራሲያዊነትን የመፃረር አቋም ስለሚሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፣ አይገባምም!

በእነዚህ መሰረታዊ የሰላም እና የዴሞክራሲያዊ ሒደት ጉዳዮች ላይ የማይስማማ ኃይል የሚኖር ከሆነም ከእንዲህ አይነቱ ኃይል ጋር ጐራ ለይቶ መታገል እንጅ መተባበር አስፈላጊ ስለማይሆን ከዚህ አጀንዳ የሚነጠሉ የፖለቲካ ኃይሎች ቢኖሩ መነጠላቸው እንደ ጉዳት ሊታይ አይገባውም። የሰላም እና የዴሞክራሲ ሒደት አጀንዳን መቃዎም እንኳንስ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ለሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች ‘ከጦርነትና ከግጭት እጠቀማለሁ!’ ብሎ ለሚባዝነው ለብልፅግና አገዛዝም ትልቅ ፈተና እና አጣብቂኝ የሚፈጥር አጀንዳ ነው። በአጠቃላይ እንዲህ

*አይነቱ ለሰላም እና ለዴሞክራሲ ሒደት ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጥ የትግል የመተባበሪያ አጀንዳ- አፈንጋጭ የሆኑ የፖለቲካ ኃይሎችን ምክንያት በማሳጣት፣ የአገዛዙን አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ በብቃት በማምከን፣ ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ በማስገኘት እና ከሁሉም በላይ ሕዝባዊ ድጋፍ በማስገኘት ረገድ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል።*

ስለሆነም ከእነዚህ ህልውናን ለማዳን የግድ ከሚያስፈልጉን አጀንዳዎች ውጭ ያሉ ሌሎች አጀንዳዎችን በተናጠል ይዘን እና ለወደፊቱ የአገራዊ የውይይት እና የድርድር ሒደት (አውድሒ) ወደ ጐን አቆይተን- "ሰላም እና ዴሞክራሲ በአዲስ የሽግግር ሒደት" በሚል ምጥን የመታገያ አጀንዳ ሁሉም የተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች ታላቅ ጥምረት በአስቸኳይ ፈጥረን ጠንካራ ትግል በማካሄድ አገራችንን ከመፍረስ፣ ሕዝባችንን ከባሰ እልቂት ልንታደግ ይገባል። ይህንን አጀንዳ በእርግጠኛነት ለማሳካት የምንችለውም 'ከግጭትና ከጦርነት እጠቀማለሁ!' ብሎ ለሚያስበው የብልፅግና አገዛዝ ጥያቄ በማቅረብ ሳይሆን አስማሚ የጋራ መታገያ አጀንዳ እና የጠራ የመዳረሻ ግብ ባለው ጠንካራ ትግል እና መስዋዕትነት ነው። ስለሆነም በእነዚህ ምጥን የትግል መተባበሪያ አጀንዳዎች አማካኝነት ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የድርጅቶች ጥምረቶች በፍጥነት መፍጠር እና የሕዝቡን ትግል በብቃት ማስተባበርና መምራት ይጠበቅብናል። ቀዳሚው፣ ዋናው እና ቀጣዩ ትኩረታችን ይህ ሊሆን ይገባል። **"ለጋራ የህልውና አደጋ የጋራ መድህን መሻት"** በሚል ርዕስ የሚካሄደው ሁለተኛው ዙር ውይይትም በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ አተኩሮ በቅርቡ የሚካሄድ ይሆናል።

ልደቱ አያሌው
የአብሮነታችን የውይይት ሒደት አስተባባሪ
ሐምሌ 28 ቀን 2016 ዓ.ም